# የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር የ2016 በጀት ዓመት

# የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማጠቃለያ ድርሞ /Executive Summary/

**ምዝገባ፡-** የጡረታ ሽፋንን ለማሳደግ ከሚሠሩት ዋና ዋና ሥራዎች መካከል የግል ድርጅቶችንና ሠራተኞቻቸውን በመመዝገብ የዐቅድ አባልነት ካርድ መስጠት ነው። በዚሁ መሰረት ወደ ዐቅዱ ሽፋን 17,228 ድርጅቶችንና 149,843 ሠራተኞችን ለመመዝገብ ታቅዶ ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ከገቢዎች ሚኒስቴር እና ከባንኮች ጋር በተደረገው የቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓት መፈጠር ከታቀደው በላይ 18,747 ድርጅቶችን እና 166,334 ሠራተኞችን ለመመዝገብ ተችሏል። አፈጻጸሙ በድርጅት ምዝገባ 109 በመቶ ሲሆን በሠራተኛ ምዝገባ 111 በመቶ ነው። በበጀት ዓመቱም ለ18,394 ድርጅቶችና ለ163,245 ሠራተኞች የዐቅድ አባልነት ካርድ ተሰጥቷል።

**የጡረታ ፈንዱን ማዳበር፡-** የጡረታ መዋጮ አሟጦ መሰብሰብ አንዱ የአስተዳደሩ አብይ ተግባር በመሆኑ፣ በበጀት ዓመቱ ብር 25.4 ቢሊዮን የጡረታ መዋጮ ለመሰብሰብ ታቅዶ የዐቅዱ አባል ያልነበሩ ሠራተኞችን በመመዝገብና የጡረታ መዋጮ በማስከፈል፣ የሕግ አስገዳጅነት እና የመዋጮ አሰባሰብ ሥርዓት ከግብር ክሊራንስ እና ባንክ ብድር ጥያቄ ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት በመፍጠርና በዲስትሪክት እና ቅ/ጽቤቶች ጤናማ የሥራ ውድድር እንዲፈጠር ቅስቀሳ በማድረግ ጭምር ብር 28.7 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ተችሏል። አፈፃፀሙም 112 በመቶ ነው። በ2015 ከነበረው 21.3 ቢሊዮን ብር የመሰብሰብ አፈጻጸም አንፃር የ7.4ብር እና 35 መቶኛ ዕድገትም አሳይቷል።

**የድርጅቶች የጡረታ መዋጮ ኦዲት፡-**13,496 ድርጅቶችን ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ አዲሱን የኦዲት አደረጃጀት በሚገባ ወደ መሬት አውርዶ ወደ ሥራ እስከሚገባ ድረስ በነበረው መጓተት፣ በተወሰኑ አካባቢዎች በፀጥታ ችግር ምክንያት እንደልብ ተንቀሳቅሶ መሥራት ባለመቻሉ እና በድርጅቶች የኦዲት አመራረጥ ላይ ሁሉንም ዓይነት የሠራተኛ መጠን ያላቸውን ድርጅቶች አደባልቆ ከመሥራት አኳያ ክፍተት በመኖሩ (አንዳንድ ድርጅቶች ብዙ ሠራተኛ ያላቸው በመሆኑ) 10,963 ድርጅቶች ብቻ ኦዲት ተደርገዋል። አፈጻጸሙ 81 በመቶ ነው። ይህም ሆኖ ካለፉት ዓመታት የተሻለ የድርጅት ኦዲት አፈፃፀም መኖሩን መረዳት ይቻላል። ለሚቀጥለው ዓመት ግን ችግሮቹን በማሰወገድ አፈጻጸሙ የተሻለ እንዲሆን ጠንክሮ መሥራት ያስፈልጋል። በበጀት ዓመቱ ብር 861,104,035 በኦዲት የተገኘ ሲሆን፣ ከተገኘው ውስጥ ብር 607,447,764 (71 በመቶ) ተሰብስቧል። በፀጥታ ችግር፣ በድርጅቶች የባንክ ሂሳብ ላይ በቂ ገንዘብ ባለመገኘቱ እና ከፊሎቹ በህግ አገልግሎት ክትትል ሂደት ላይ በመሆናቸው አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ሆኗል። በሕግ አስገዳጅነት፡- አስተዳደሩ ስለአሠራሩና ስለማህበራዊ ዋስትና አፈፃፀም ግንዛቤ ከማስረፅ ሥራ በተጓዳኝ የሕግ አግባብን በመከተል የጡረታ መዋጮ ገቢ እየሰበሰበ ይገኛል። በዚህ መሠረት የሚጠበቅባቸውን የጡረታ መዋጮ ባልከፈሉ የግል ድርጅቶች ዉዝፍ የጡረታ መዋጮ ከባንክ ሂሳብ ተቀንሶ ለፈንዱ አካዉንት ገቢ እንዲሆን ብር 519,810,497 ተጠይቆ ብር 498,814,527 ወደ ጡረታ ፈንዱ ገቢ ተደርጓል። አፈፃፀሙ 96 በመቶ ነው።

**ኢንቨስትመንት፡-**የጡረታ ፈንዱን ኢንቨስትመንት ላይ በማዋልና ትርፍ በማግኘት አስተማማኝነቱንና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ ሌላው የአስተዳደሩ ቁልፍ ተግባር ነው። ከዚህ አንፃር ኢንቨስትመንት ላይ መዋል የሚገባው ገንዘብ ሙሉ ለሙሉ ኢንቨስት የተደረገ ሲሆን፣ ብር 9,500,000,000 ትርፍ ለማግኘት ታቅዶ ብር 9,753,890,271 ተገኝቷል። አፈጻጸሙ 102 በመቶ ነው። ትርፉ የተገኘባቸው የኢንቨስትመንት መስኮች፤ ከትሬዠሪ ቢል ብር 6,719,896,410፣ ከመንግስት ቦንድ ብር 2,505,650,000፣ ከልማት ባንክ ቦንድ ብር 327,662,877፣ ከሕንጻ ኪራይ ብር 5,887,279 ፣ ከጊዜ ገደብ የባንክ ተቀማጭ ብር 187,890,411 እና ከሁለት ወራት የአበል ክፍያ የቁጠባ ተቀማጭ ወለድ ብር 6,903,294 ነዉ።

**የጡረታ አበል ውሳኔና ክፍያ፡-** በበጀት ዓመቱ 6,105 ባለመብቶች የአበል ውሳኔ ጥያቄ አቅርበው መረጃቸው ለተሟላ 6,016 (3,924 ወንድ እና 2,127 ሴት) ባለመብቶች የአበል ውሳኔ እና ክፍያ ትእዛዝ ተዘጋጅቶ ክፍያውን እንዲያገኙ

ተደርጓል። ከበጀት ዓመቱ በፊት 249 ባለመብቶች ጥያቄ አቅርበው በዚህ በጀት ዓመት ውስጥ ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ፣ በአጠቃላይ 6,300 (4,151 ወንድ እና 2,149 ሴት) ባለመብቶች ውሳኔና ክፍያ አግኝተዋል። መረጃ ያሟሉት ባለመብቶች በሙሉ ውሳኔ ያገኙ በመሆኑ አፈፃፀሙ 100 በመቶ ተሳክቷል። በበጀት ዓመቱ የጡረታ አበል ክፍያ ማሻሻያ በመደረጉ በባለመብቱ ላይ ከፍተኛ ደስታ ፈጥሯል። በዚህ የክፍያ ጭማሪ 65 በመቶ ባለመብቶች ከድህነት ወለል የወጡ ሲሆን አስተዳደሩም ብር 398,484,272 ተጨማሪ ወጪ አድርጓል።

**የሰው ሀብት አስተዳደር እና ልማት፡-**

በአስተዳደሩ ባለፈው በበጀት ዓመቱ በተለያዩ መደቦች ላይ የሠራተኞችን ቅጥር ፈፅሟል። በዘህ መሠረት ወንድ 108 ሴት 55 ድምር 163 ሠራተኞች ተቀጥረዋል። ወንድ 13 ሴት 8 በድምሩ 21 ሠራተኞች የደረጃ ዕድገት ተሰጥቷል። ወንድ 17 ሴት 22 በድምሩ 39 ሠራተኞች ዝውውር ተፈፅሟል። ወንድ 40 ሴት 16 በድምሩ 56 ሠራተኞች ተሰናብተዋል። የለቀቁበት ምክንያት በጡረታ 17፣ በሞት 1፣ በዲስፕሊን 1፣ በራስ ፈቃድ 37 ሲሆን የሥራ ደረጃቸውም በባለሙያ 32፣ ከባለሙያ በታች 24 ሠራተኞች ተሰናብተዋል።
ዓመታዊ የሰው ሀብት ፍልሰት 56/1755 = 3.19% ሲሆን የፍልሰት መጠኑ ዝቅተኛ መሆኑ ያመለካታል። ፍልሰቱ በ2015 ከነበረዉ 4.23 በመቶ ጋር ስነፃፀር የ 1.04 በመቶ ቅናሽ ያሳዩ ሲሆን በጥናት እንደ በጎ ጎን ከተቀመጠዉ የ10.4 በመቶ የተቋማት የሠራተኛ ፍልሰት ጋር ስታይ አስተዳደሩ የተረጋጋ የሥራ አካባቢ እንዳለ ያመላክታል።
ሥልጠናን በተመለከተ በመቀሌ፣ አዳማ፣ ጅማ፣ ድሬደዋ፣ ኮምቦልቻ፣ በሐዋሳ፣ አ.አ.፣ ሸገር እና ነቀምት በአስሩ ዲስትሪክቶች በዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ም/ሥራ አስፈጻሚዎች በለውጥ አመራር፣ በስትራቴጅክ ዕቅድ፣ በኮርፖሬት ገቨርናንስ፣ በሠራተኞች አስተዳደር፣ በግዥ መመሪያ እና በኦፕሬሽን ሥራዎች አተገባበር ዙሪያ ለ320 ሴት እና 460 ወንድ በድምሩ ለ780 አመራሮችና ሲኒየር ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

**የበጀት አፈፃፀም፡-** በበጀት ዓመቱ ለደመወዝ፣ ጡረታ እና ቋሚ አበል ብር 387,378,834፣ ለሥራ ማስኬጃ ብር 308,804,754፣ ለጡረታ አበል ክፍያ ብር 2,394,766,637፣ ለካፒታል በጀት ብር 671,371,746፣ መጠባበቂያ 320,796,091 በድምሩ ብር 4,083,118,063 ሥራ ላይ እንዲውል ታቅዶ ለደመወዝ፣ ጡረታ እና ቋሚ አበል ብር 353,236,361 (91%)፣ ሥራ ማስኬጃ ብር 257,658,118 (83%)፣ ለጡረታ አበል ክፍያ ብር 2,279,023,920

(95%)፣ ለካፒታል በጀት ብር 204,340,007(30%) ከመጠባበቂያ ብር 48,926,148 (15%) በድምሩ ብር 3,094,258,406(76%) ሥራ ላይ ውሏል። የበጀት ዝርዝር አፈጻጸም በበጀት ሪፖርት ላይ ተመላክቷል።